በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ታህሳስ 4 ቀን 2012
አዲስ አበባ

# 77ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 77ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአትን ለመደንገግ በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር ረቂቅ አዋጅ ዋና አላማ የመንግስት አካላት በመንግስት ፕሮጀክቶች ውስጥ ያላቸውን ሃላፊነት በግልጽ በማመላከት ተጠያቂነትን እና ግልጸኝነትን በማስፈን የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡ በሀገራችን ወጥ የሆነ የመንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአት ባለመኖሩ ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪ እና ጥራት ባለመጠናቀቃቸው የሀገሪቱን ውስን ሀብት ለከፍተኛ ብክነት እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ችግሩን ለመቅረፍ የሚያስችል ወጥ የሆነ የፌዴራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ስርአትን በህግ ለመደንገግ የፕላንና ልማት ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅ እና ባዮፊውል ኮርፖሬሽን እንደገና ለማቋቋም የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለማዕድን እና ለነዳጅ ሀብት መንግስት የሰጠውን ልዩ ትኩረት ተከትሎ በሂደት የታዩ ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባሮችን አካቶ እንዲሰራ እና አደረጃጀቱም ይህንኑ በሚያግዝ መልኩ እንዲደራጅ ለማድረግ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ም/ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ከተወያየ በኋላ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

3. በውጭ አገራት ስለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠትና የመፈጸም ስምምነትን ለማጽደቅ የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ሌላው በም/ቤቱ የታዩ ጉዳይ ነው፡፡ በውጭ አገራት

ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጅ ኢትዮጵያ ማጽደቋ የውጭ ባለሀብቶችን ስጋቶች የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ የውል አፈጻጸሞችን ቀልጣፋ የሚያደርግ ነው፡፡ ወደ አገራችን የሚኖረው የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር የስምምነቱ መጽደቅ አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ የጠቅላይ አቃቤ ህግ ስምምነቱን ለማጽደቅ ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

4. በመጨረሻም ም/ቤቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረቡትን የተለያዩ ስምምነቶች እና የማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጆቹ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

//